# ዓባይ ልገደብ አለ

ተኮላ መኮንን
TEKOLA MEKONEN
tekolamekonen@yahoo.com

የዓመታት ጉዞ ታሪኩን ለቅሶውን እያስታወሰ፣
ወላጁን እየናፈቀ ዝንተ ዓለም እየፈሰሰ፣
የተራራ ላይ ስንቁን አፈሩን፡ እየገመሰ፣
ለወገቡ መደገፊያ ዛፍ ምርኩዙን፡ እያጋበሰ፣
ዓባይ የጣና ውልዱ ጎረቤት አገር ገሰገሰ፣
እረጅሙን ጉዞ ተያያዘው ላይመለስ ቁልቁል ፈሰሰ።

ስደተኛው ጥቁር ዓባይ ወደ ካርቱም አመራ፣
የግብጦችን ውሃ ጥም ሊቆርጥ ከተማቸውን ሊያበራ፣
ለራሱ ሰቀላ ሳይኖረው ለባእድ እልፍኝ ሊሠራ፣
የዘመድ እረሃብ እረስቶ ለውጭ አዝመራ ሊዘራ።

ዓባይ የማያረጅ ዓባይ የጣና ጎረምሳ፣
ከእንቅልፉ ነቃ ልበል ዛሬ? ዘመድ ብሎ ተነሳ።
ሳትበሉ አላበላም ብሎ፣
ቤቱን ሳያሸንፍ ጎረቤት ላይጋብዝ ምሎ።

ተነሳ ዓባይ ኩሬ ሊሠራ ለጎረቤት ያደረገውን ሊደግም፣
በግድብ ድልድይ ውስጥ አልፎ አሁንም ወደፊት ሊያዘግም።
በመስኖ እያዳረሰ አካባቢውን አጠጥቶ፣
ደህና ስንብቱ ሊለን ላገሩ ብርሃን አብርቶ።

ዓባይ መንገድ ለጠፋው መሪ ዓባይ የማይመጣ ሰው፣
መሄዴ ካልቀረ ብሎ መንደር ሰፈሩን አቃመሰው፣
ወገቡን ሸብ አድርጎ ብርሃን ሞገሱን አላበሰው።
በነፃ ሲጋብዝ እንዳልኖረ ዛሬ ዘመዶቹን ናፍቆ፣
ክፈሏቸው ማለት ጀመረ በችግራቸው ተጨንቆ።

እናቱን የማይረዳ ልጅ እርግማን አለበት ብሎ አምኖ፣
ከውጭ የመጣ ገንዘብ ሳይኖረው በዘመድ ቤተሰብ ተማምኖ፣
አገሩን ሊረዳ ተነሳ በግድብ ሊያልፍ ወስኖ።
መሄዴ ካልቀረ ልስጣችሁ አለ ያለኝን ላካፍላችሁ፣
አልመጣም ዳግም አንተያይ ተርባችሁ ግን አልተዋችሁ፣
ተጓዥ ነኝ አልሸከረከር ተጠምታችሁ አላልፍ ትቻቺሁ።

መረዳዳቱ መልካም ነው አለ በልጅ አዋቂው ኮርቶ፣
ዓባይ ለልማት ተነሳ በዘመድ እውቀት ተመክቶ።

ዓባይ የምዬ ኢትዮጵያ ለቅሶ፣
ዓባይ የጣና ምሰሶ፣
ዛሬ ድንገት ባኖ ተነሳ ለዘመናት በነፃ ፈሶ።
የተንጣለለው ዓባይ የሱዳን የግብጥ ደመራ፣
ፊቱን መለሰ ዛሬ ባገሩ ቤት ሊሠራ፣
ዘመድ አዝማድ ወላጆቹን ካጽናፍ አጽናፍ ሊያኩራራ!!

በቁርጠኛነት ተነስቶ ዓባይ በቃኝ ልገደብ አለ፣
ለሁሉም እንደሚበቃ ላመነው ሁሉ እየማለ፣
ላሳደጉኝ ዋጋ ልክፈል ላጠቡኝ ላጥባቸው አለ።